MY SCHOOL DC
The Public School Lottery

# My School DC ማመልከቻ ቅጽ አሞላል መምሪያ።

**ዓላማ፡** የዚህ መመሪያ ዋና ዓላማ የMy School DC ኦንላይን ማመልከቻ ቅጽ እንዴት እንደሚሞሉ አስፈላጊውን እርዳታ ለመስጠት ነው። በኦንላይን በሚያመለክቱበት ወቅት እባክዎ ይህንን መመሪያ በጥንቃቄ ተከተሉ። ማመልከቻው በእንግሊዘኛ እና በእስፓኒሽ ቋንቋዎች በMySchoolDC.org ድህረ ገጽ ላይ ይገኛል። ይህ መምሪያ በተለይ በእንግሊዘኛ ለተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ማብራሪያ የሚሰጥ ነው።

እባክዎ ይህ መመሪያ በMySchoolDC.org ድህረ ገጽ ላይ የሚገኘው ማመልከቻው ቅጽ ምትክ እንዳልሆነ ይረዱ።

በኦንላይን የሚገኘውን የማመልከቻ ቅጽ ለመሙላት እርዳታ ካስፈለገዎ እባክዎ በMy School DC አፋጣን መስመር በ(202) 888-6336 ከሰኞ እስከ አርብ ባሉት ቀናት ከ8am እስከ 5pm ይደውሉ። ሰራተኞች በራስዎ ቋንቋ አስተርጓሚ በማቅረብ እና ማመልከቻ በስልክ ለመሙላት እርዳታ ለመስጠት ዝግጁ ሆነው ይጠብቃሉ። አስተርጓሚም በቀጥታ ተመድብዎሎት በስልክ እርዳታ በመሰጠት አማካይነት የማመልከቻው ቅጽ በተሟላ ሁኔታ አጠናቀው መላክ እንዲችሉ ያስችልዎታል።

---

## ማውጫ


ማውጫ ........ 1

ደረጃ 1፡ የ የትምህርት ዓመት የ My School DC ኦንላንይ ማመልከቻ ማግኘት ........ 2

ደረጃ 2፡ አካውንት ይፍጠሩ........ 3

ደረጃ 3፡ ማመልከቻውን ይጀምሩ ........ 6

ደረጃ 4፡ የተማሪን መረጃ ማስገባት ........ 7

ደረጃ 5፡ የወንድም/እህት ምርጫ መረጃን ማስገባት ........ 9

የስህተት መልዕክቶች እና ማሳወቂያዎች........ 10

ደረጃ 6፡ የዋናው አሳዳጊን መረጃ ማስገባት ........ 13

ደረጃ 7፡ ትምህርት ቤቶችን መምረጥ ........ 17

ደረጃ 8፡ የ DCPS ምርጥ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና መርሀግብሮች........ 19

ደረጃ 9፡ የትምህርት ቤት ምርጫዎን ቅደም ተከተል መስጠት ........ 21

ደረጃ 10፡ ማረጋገጥና ማስገባት........ 23


ማመልከቻዎን ማረም ........ 27

የገቡ ማመልከቻዎች ........ 29

## ደረጃ 1፡ የ የትምህርት ዓመት የ My School DC ኦንላንይ ማመልከቻ ማግኘት


የMy School DC የኦንላይን ማመልከቻ በሦስት መንገዶች ማግኘት ይችላሉ።

1. MySchoolDC.org ድህረ ገጽ ውስጥ ገብተው በገጹ አናት ላይ ባለው ቀይ ምናሌ ላይ "ያመልክቱ" የሚለውን ጠቅ ያድርጉ፣
2. MySchoolDC.org ድህረ ገጽ ውስጥ በመግባት የመጀመሪያው ገጽ ላይ "ወደ ማመልከቻ ይሂዱ" የሚለውን ጠቅ ያድርጉ፤
3. MySchoolDC.org ድህረ ገጽ ውስጥ በመግባት የመጀመሪያው ገጽ ላይ "ወደ ማመልከቻ ይሂዱ" የሚለውን ጠቅ ያድርጉ፤



## ደረጃ 2፡ አካውንት ይፍጠሩ

አካውንት ለመፍጠር፣ "ይጀምሩ" የሚለው ርዕስ ስር ያለው "እዚህ ይመዝገቡ" የሚለው ቀይ አዝራር ላይ ጠቅ ያድርጉ።





አመልካች አንድን አካውንት ሊፈጥር የሚችልባቸው ሁለት መንገዶች አሉ፣

- የኢሜል አድራሻ በመጠቀም መመዝገብ፤ ወይም
- የተጠቃሚ ስም መፍጠር

ከነዚህ ከሁለቱ ዘዴዎች አንዱን ብቻ መምረጥ ይችላሉ። በኢሜል አድራሻ አካውንት መፍጠሩ በበለጠ የተሻለ ነው።

**ዘዴ 1፡ "የኢሜል አድራሻ በመጠቀም ይመዝግቡ"**




**ደረጃዎች**

1. የኢሜል አድራሻዎን ያስገቡ.
2. የኢሜል አድራሻዎን ትክክለኛነቱን ያረጋግጡ.
3. የኢሜል አድራሻዎን ትክክለኛነቱን ያረጋግጡ.


    **ማስታወሻ፣ መመዝገብዎን ለማረጋገጥ እባክዎን ከmyschooldc@dc.gov. የተላከ የኢሜል መልእክት ይመልከቱ። በሰኮንዶች ውስጥ መድረስ አለበት። በኢሜይሉ ያለውን ሊንክ በመጫን ወደዚህ ሳይት ተመልሰው የመግቢያ መታወቂያ ይፍጠሩ። ወዲያውኑ ማመልከቻዎን መጀመር ይችላሉ። ከmyschooldc@dc.gov የኢሜል መለእክት ካልደረሰዎት በ202-888-6336 ይደውሉ።**.


4. መመዝገብዎን እንዳረጋገጡ የመግቢያ ኮድ ይፍጠሩ። የመግቢያ ኮዱ ስምንት ፊደላት የያዘ መሆን አለበት።.
5. የመግቢያው ኮድ ትክክል መሆኑን ያረጋገጡ።.
6. በስተቀኝ በኩል ወረድ ብለው "አስገባ" የሚለውን ይጫኑ.




**ዘዴ 2፡ የተጠቃሚውን ስም በመጠቀም  አካውንት መፍጠር**

"ኢሜይል አድራሻ የለኝም" የሚለውን አገናኝ ይጫኑ







**ደረጃዎች**


1. የተጠቃሚ ስምዎን ያስገቡ። የተጠቃሚ ስም ለመፍጠር ፊደላትን፣ቁጥሮችን፣ወይም ሁለቱንም የያዘ ሊሆን ይችላል። የተፈጠረውን የተጠቃሚ ስም ጽፈው በማስታወሻዎ ይያዙት።
2. የተጠቃሚ ስምዎን ያረጋግጡ።.
3. ሁለት ሚስጥራዊ ጥያቄዎች ከተዘረዘሩት ጥያቄዎች ይምረጡ። ከሚከተሉት ሁለቱን ጥያቄዎች መመለስ ያስፈልግዎታል።:
   a. የሴት አያትዎ ስም ማነው?
   b. የእናትዎ አባት ስም ማነው?
   c. የትኛውን ፊልም ነው የሚወዱት?
   d. የሚወዱት ቀለም የትኛውን ነው?
   e. የሚወዱት የአይስክሬም ጣዕም ምንድነው?
4. ለመጀመሪያውና ለሁለተኛው ሚስጥራዊ ጥያቄዎች መልስዎችዎን ይጻፉ። እባክዎን የተጠቀሟቸውን ሚስጥራዊ ጥያቄዎችን ምላሽ ይፃፉ፣ እና ለራስዎ ለማስታወሻ ያስቀምጡት።
5. የመግቢያ ኮድ ይፍጠሩ። ከዱ 8 ፊደላት የያዘ መሆን አለበት። እባክዎን የፈጠሩትን የመግቢያ ኮድ ይፃፉ፣ እና ጽፈው ለራስዎ ማስታወሻ ያስቀምጡ።
6. የመግቢያ ኮድዎን ያረጋግጡ.
7. በስተቀኝ በኩል ወረድ ብለው "አስገባ" የሚለውን ይጫኑ.

## ደረጃ 3፡ ማመልከቻውን ይጀምሩ

ዲስ ማመልከቻ ለመጀመር፣ በገጹ አናት ግራ ጥግ ላይ ቀዩን "ማመልከቻ ይጀምሩ" አዝራርን ጠቅ ያድርጉ።.



## ደረጃ 4፡ የተማሪን መረጃ ማስገባት




**ደረጃዎች**

1. የተማሪው የመጀመሪያ ስም
2. <u>በፍላጎት የሚደረግ፡ የተማሪው የአባት ስም</u>
3. የተማሪው የአያት ስም
4. የተማሪው የልደት ቀን (ወር/ቀን/ዓመት)**ማስታወሻ፤** መጀመሪያ ወሩን፣ ቀጥሎ ቀኑን፣ ከዚያ ቀጥሎ ዓመተ ምህረቱን
    a. የልደት ቀን ካስገቡ በኋላ፣ "ይህ ማለት ተማሪዎ ዕድሜው__ዓመት ነው" የሚለው ዓረፍተ ነገር ከገባው ቀን በታች ይታያል። እባክዎን ዕድሜው ከልጅዎ ትክክለኛ ዕድሜ ጋር የሚዛመድ መሆኑን ያረጋግጡ።
5. የተማሪው ጾታ
    a. ሴት
    b. ወንድ
    c. አሃዝ ያልሆነ (NB)
    d. የማያረጋግጥ (NC)
    e. ላለመናገር እመርጣለሁኝ (X)


6. የአሁኑ የክፍል ደረጃ
7. የአሁኑ ትምህርት ቤት
    a. የልጅዎን ት/ቤት ካላገኙ "ሌላ" የሚለውን መምረጥ ይኖርብዎታል። የትምህርት ቤቱን ስም፣ አድራሻ እና የስልክ ቁጥር እንዲያስገቡ ይጠየቃሉ።
    b. ልጅዎ በአሁኑ ጊዜ በ DCPS ወይም በቻርተር ትምህርት ቤት የሚማር ከሆነ የተማሪው የመታወቂያ ቁጥር የሚል

ጽሁፍ ያያሉ። ይህንን ጽሁፍ ማየት የሚችሉት ልጅዎ በአሁኑ ወቅት በDCPS ወይም በቻርተር ትምህርት ቤት የሚማር ከሆነ ብቻ ነው። የተማሪው መታወቂያ በራስ-ሰር ሊገባ ይችላል። ካልገባ፣ እባክዎ የተማሪዎን የመታወቂያ ቁጥር ያስገቡ። ቁጥሩን የማያውቁ ከሆነ ወደ My School DC ነጻ የስልክ መስመር በ(202) 888-6336 ይደውሉ። በተጨማሪም የልጅዎን የDC One Card ቁጥር መጠቀም ይችላሉ።


8. የመጪው ጸደይ የክፍል ደረጃ

## ደረጃ 5፡ የወንድም/እህት ምርጫ መረጃን ማስገባት

"ተማሪው በDCPS እና/ወይም ቻርተር ትምህርት ቤት የሚማሩ ወንድሞች/እህቶች አሉት?" ለሚለው ጥያቄ መልስ ይስጡ




መልሱ "አይ" ከሆነ፣ ከታች በስተቀኝ ጥግ ላይ ያለውን "ያስገቡ እና ይቀጥሉ" አዝራርን ጠቅ ያድርጉ፣ ወይም ከዚህ ማመልከቻ ለመውጣት እና በሌላ ጊዜ እንዲቀጥል ለማድረግ "ያስገቡ እና ቆይተው እንደገና ይመለሱ" የሚለውን ጠቅ ማድረግ ይችላሉ።




መልሱ "አዎ" ከሆነ ከዚህ በታች የሚከተለውን መረጃ ያስገቡ።

**የወንድም/እህት መረጃ**

1. የወንድም/እህት የመጀመሪያ ስም
2. የወንድም/እህት የመጨረሻ ስም
3. የወንድም/እህት የአሁኑ የክፍል ደረጃ
4. የወንድም/እህት የአሁኑ ትምህርት ቤት
    a. ወንድምየው/እህትየው በአሁኑ ጊዜ በDCPS ትምህርት ቤት የሚማሩ ከሆነ የተማሪ የመታወቂያ ቁጥር የሚል ጽሁፍ ይታያል። ቤተሰቡ የወንድምየው/እህትየውን የተማሪ መታወቂያ ቁጥር የሚያውቁት ከሆነ፣ ሊያስገቡት ይገባል። ይህ በፍላጎት የሚገለጽ መስክ ነው።


ማስታወሻ፡ አመልካቹ በDCPS እና/ወይም ቻርተር ትምህርት ቤት የሚማሩ ከአንድ በላይ ወንድሞች/እህቶች ካሉት፣ “ወንድም/እህት ያክሉ” በሚለው ሊንክ ላይ ጠቅ በማድረግ ለተጨማሪዎቹ ወንድሞች/እህቶች መረጃን ማቅረብ ይችላሉ።

5. የወንድም/እህት መረጃ ማስገባትን ካጠናቀቁ በኋላ ወደ ቀጣዩ ክፍል ለመሄድ "ያስገቡ እና ይቀጥሉ" የሚለውን ጠቅ ማድረግ አለበለዚያ ከዚህ ማመልከቻ ለመውጣት እና በሌላ ጊዜ ለመቀጠል "ያስገቡ እና ቆይተው እንደገና ይመለሱ" የሚለውን ይጫኑ።

## የስህተት መልዕክቶች እና ማሳወቂያዎች

“ያስገቡ እና ይቀጥሉ” ወይም “አስቀምጥ እና በኋላ ተመለሰው ያስገቡ እና ቆይተው እንደገና ይመለሱ” የሚለው ላይ ጠቅ ሲያደርጉ የሚከተሉት መልዕክቶች ብቅ ሊሉ ይችላሉ።

**የስህተት መልዕክት 1. የተማሪ መታወቂያ ማሳወቂያ - ስሪት 1:**
የተማሪውን መታወቂያ ካላስገቡ የሚከተሉትን መልእክቶች ያያሉ፤





ይህ መልእክት የሚለው፤ "እባክዎ የተማሪውን መታወቂያ ቁጥር ያስገቡ። ስለዚህ ቁጥር ለማወቅ እና የት ሊያገኙት እንደሚችሉ ይህንን ይጫኑ። አሁንም የልጅዎን የተማሪ መታወቂያ ቁጥር ማግኘት ተቸግረዋል? በMy School DC Hotline የስልክ መስመር ቁጥር (202) 888-6336 ከሰኞ እስከ አርብ ባሉት ቀናት ከ8 a.m. እስከ 5 p.m መደወል ውይም በinfo.myschooldc@dc.gov ኢሜል ቢያደርጉልን ልንረዳዎት እንችላለን።”

ይህንን መልእክት ካዩ ሁለት አማራጮች አሉዎት፤:

a. የልጅዎን መታወቂያ ቁጥር ለማስገባት የተማሪው መታወቂያ ይጫኑ።

b. ማመልከቻውን ለመቀጠል “ያለ ተማሪ መታወቂያ ቀጥል” የሚለውን ይጫኑ። ይህንን መረጃ ለማግኘት ማመልከቻዎን ከማስገባትዎ በፊት በMy School DC ነጻ የስልክ መስመር በ202) 888-6336 እንዲደውሉ በጥብቅ እናስጠነቅቃለን።
   - ማስታወሻ፤ ይህን አማራጭ ከመረጡና ልጅዎ ምርጥ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም መርሀግብር ለመግባት የሚያመለክት ከሆነ መደበኛ ውጤቶቻቸው በድረ ገጽ ላይ ስለማይታዩ መረጃውን እራስዎ መስጠት አለብዎት።

**የስህተት መልዕክት 1. የተማሪ መታወቂያ ማሳወቂያ - ስሪት 2:**
የተሳሳተ የተማሪው መታወቂያ ቁጥር ካስገቡ የሚከተለውን መልእክት ያያሉ፤




ይህ መልእክት የሚለው፤ "እናዝናለን። ያስገቡት የተማሪ መረጃ ልናውቀው አልቻልንም። እባክዎ የተማሪውን መታወቂያ ቁጥር፣ ስሙ እና የትውልድ ዘመን በትክክል መግባታቸውን ያረጋግጡ። ይህንን መልእክት በተደጋጋሚ ከደረሰዎት የMy School DC Hotline መስመር በ(202) 888-6336 ከሰኞ እስከ አርብ ባሉት ቀናት ከ8 a.m እስከ 5 p.m ደውለው ይጠይቁ። ወይም በኢሜል info.myschooldc@dc.govጽፈው ይጠይቁ።"


ይህንን መልእክት ካዩ ሁለት አማራጮች አሉዎት፤

a. የMy School DC Hotline መስመር በ(202) 888-6336 ደውለው የልጅዎ የተማሪ መታወቂያ ቁጥር ትክክል መሆኑን ያረጋግጡ። ትክክለኛውን መረጃ እንዳገኙ የተማሪ መታወቂያ ቁጥርን ለማረም "ሁለቱ ፈትሽ/ያስገባሁትን አርትዕ አድርግ" የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።
b. የተማሪው መታወቂያ ቁጥር ትክክል መሆኑን ሳያረጋግጡ ባስገቡት መረጃ መቀጠል ከፈለጉ "ከመረጃው ጋር እንዳለ ቀጥል" የሚለውን ይጫኑ።

**ማስታወሻ፡-** ይህን አማራጭ ከመረጡና ልጅዎ ምርጥ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም መርሀግብር ለመግባት የሚያመለክት ከሆነ መደበኛ ውጤቶቻቸው በድረ ገጽ ላይ ስለማይታዩ መረጃውን እራስዎ መስጠት አለብዎት።

**የስህተት መልዕክት 3. የተባዛ ማመልከቻ ማሳወቂያ - ስሪት 1**

በአካውንትዎ ውስጥ ለተመሳሳይ ልጅ ቀደም ብለው ማመልከቻ ጀምረው ከሆነ፣ የሚከተለውን የስህተት መልዕክት ያያሉ፤





መልዕክቱ የሚለው፣ "እናዝናለን፣ እንደተገነዘብነው ከሆነ በዚህ ተማሪ ስም የማመልከቻ ቅጽ ተፈጥሯል። ይህንን የማመልከቻ ቅጽ ለማስተካከል/ለማረም ከፈለጉ እባክዎን ይህን መስኮት ይዝጉ እና በየእኔ ማመልከቻዎች ገጽ ላይ ከነበርዎት ማመልከቻዎች አጠገብ ማመልከቻዎን ያርሙ የሚለውን ጠቅ ያድርጉ። "

"ይህን መልዕክት ዝጋ እና ወደ የእኔን ማመልከቻዎች ገጽ ተመለስ" የሚለውን አዝራር ጠቅ ማድረግ አለብዎ፣ ከዚያ ነባሩን ማመልከቻዎን ማግኘት ወደሚችሉበት ወደ የእኔ ማመልከቻዎች ገጽ ይወሰዳሉ።

**የስህተት መልዕክት 3. የተባዛ ማመልከቻ ማሳወቂያ - ስሪት 2**

ለዚህ ተማሪ በሌላ አካውንት (መዝገብ) በኩል አስቀድሞ የማመልከቻ ቅጽ ተከፍቶ ከሆነ፣ የሚከተለውን የስህተት መልዕክት ያያሉ፡





መልዕክቱ የሚለው፣ "እናዝናለን፤ እንዳስተዋልነው ከሆነ በዚህ ተማሪ ስም አንድ የማመልከቻ ቅጽ በሌላ አካውንት (መዝገብ) የተከፈተ መሆኑን ተገንዝበናል። ይህንን የማመልከቻ ቅጽ ማግኘት ከፈለጉ በMy School DC ነጻ የስልክ መስመር (202) 888-6336 በመጠቀም ከሰኞ እስከ አርብ ባሉት ቀናት ከ8 a.m እስከ 5 p.m ባሉት ጊዜያት ደውለው ይጠይቁ። ወይም በኢሜል info.myschooldc@dc.gov መልእክት በመላክ ይጠይቁ። ለአንድ ተማሪ አንድ ማመልከቻ ማስገባት ብቻ ነው የሚፈቀደው። በአንድ ተማሪ ስም ተደጋጋሚ ማመልከቻ በዚያው ወቅት ከደረሰ የMy School DC የስራ ባልደረባ ሎተሪ ከመውጣቱ በፊት አንዱን ማመልከቻ ብቻ አስቀረቶ ሌሎችን ከዳታው መዝገብ ያስወግዳል።"

ማመልከቻውን ለመቀጠል "ቀጥል" የሚለውን መጫን ይችላሉ ወይም ለመውጣት "ከማመልከቻ ውጣ" የሚለውን መጫን ይችላሉ። እባክዎ በMy School DC ነጻ የስልክ መስመር (202) 888-6336 ለተጨማሪ እርዳታ ደውሉልን።


**የዕድሜ መስፈርት ማሳወቂያዎች**

ልጅዎ በእድሜያቸው መሰረት ለመከታተል ብቁ ከሆኑበት ዝቅ ወዳለ ደረጃ የሚያመለክቱ ከሆነ ከሚከተሉት የስህተት መልዕክቶች ውስጥ አንዱን ሊያገኙ ይችላሉ። መልስዎ "አይ" ከሆነ "የለም" የሚለውን ይጫኑ፤ መልስዎ አዎ ከሆነ "አዎ" የሚለውን ይጫኑ።


**የስህተት መልዕክት፡"ለPK3 አመልክተዋል። በልጅዎ ዕድሜ መሠረት ለPK4 ብቁ ነው። የክፍል ደረጃውን ወደ PK4 ከፍ ማድረግ ይፈልጋሉ?"**





**የስህተት መልዕክት፡ "ለPK3 አመልክተዋል። በልጅዎ ዕድሜ መሠረት ለመዋዕለ ህፃናት ብቁ ነው። የክፍል ደረጃውን ወደ PK4 ከፍ ማድረግ ይፈልጋሉ?"**




**የስህተት መልዕክት፡ ለPK3 አመልክተዋል። በልጅዎ ዕድሜ መሠረት ለመዋዕለ ህፃናት ብቁ ነው። የክፍል ደረጃውን ወደ መዋዕለ ህፃናት ከፍ ማድረግ ይፈልጋሉ?**





**የስህተት መልዕክት፡ "ለPK4 አመልክተዋል። በልጅዎ ዕድሜ መሠረት ለመዋዕለ ህፃናት ብቁ ነው። የክፍል ደረጃውን ወደ መዋዕለ ህፃናት መለወጥ ይፈልጋሉ?"**



## ደረጃ 6፡ የዋናው አሳዳጊን መረጃ ማስገባት

ይህ ሰው ተማሪው በዋነኝነት የሚኖርበት ህጋዊ አሳዳጊ መሆን አለበት። የአሳዳጊው አድራሻ ለተማሪው የክልልንና የቅርበት ምርጫዎችን ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ ይውላል። የDC ነዋሪ ካልሆኑ፣ በDCPS ትምህርት ቤቶች ውስጥ የክልል ወይም የቅርበት አማራጮችን አይቀበሉም።




**STEPS**

1. የመጀመሪያ ስም
2. የመጨረሻ ስም

3. ተመራጭ ቋንቋ

- እንግሊዝኛ
- ስፓንኛ
- ፈረንሳይኛ
- ካንቶኒስኛ
- ማንዳሪንኛ
- ቬትናሚሴ
- አማርኛ
- የአሜሪካ የምልክት ቋንቋ (ኤኤስኤል)
- ሌላ

**ማስታወሻ፡** በአሳዳጊው የተመረጠውን ቋንቋ እዚህ ያመልክቱ። My School DC ከቤተሰቶች ጋር የተሻለ ውይይት የሚያደርግበት ስለሆነ ይህ አስፈላጊ መረጃ ነው።

4. የስልክ ቁጥር #1
   a. አንዴ የስልክ ቁጥር ካስገቡ በኋላ "ይህ የሞባይል ስልክ ነው?" ብለው ይጠየቃሉ። አዎ ወይንም አይ ብለው ይመልሱ።
   b. ለቀዳሚው ጥያቄ "አዎ" ብለው ከመለሱ፣ "አዎ፣ ስለ ማመልከቻዎቼ የጽሑፍ ማሳወቂያዎች መቀበል እፈልጋለሁ" የሚለው ሳጥን አጠገብ ምልክት በማድረግ ማመልከቻዎን የተመለከቱ የጽሑፍ ማሳወቂያዎችን ለመቀበል መምረጥ ወይም ሳጥኑ ላይ ምልክት ባለማድረግ በምርጫዎ መተው ይችላሉ።
5. <u>በፍላጎት የሚደረግ፡ የስልክ ቁጥር #2</u>
6. <u>በፍላጎት የሚደረግ፡ የኢሜል አድራሻ</u>
7. የመንገድ አድራሻ
8. <u>በፍላጎት የሚደረግ፡ አፓርትማ #/ ሱት#/ ዩኒት#</u>
9. ከተማ
10. ግዛት
11. ዚፕ ኮድ

እንደአጋጣሚ አድራሻዎን በሚያስገቡበት ወቅት ስህተት የሚጠቁም መልስ ካገኙ የዚህ ምክንያቱ የዳታው መዋቅር ያስገቡትን አድራሻ ሊያውቀው ስላልቻለ ነው። መልእክቱ የሚከተሉትን ሁለት አማራጮች ይጠቁማል፤

a. ስርዓቱ ትክክል ነው ብሎ የሚያምንበትን የአድራሻ ጥቆማ
b. ያስገቡት የመጀመሪያ አድራሻ

**የስህተት መልዕክት፡ የዳታው መዋቅር የዲሲን አድራሻ ሊቀበል አይችልም። ስለዚህ ከሚቀጥሉት አማራጮች የሚስማማዎን አድራሻ ይምረጡ፤**





ከሚከተሉት አማራጮች አንዱን መውሰድ ይችላሉ፤

- የዳታው መዋቅር የተሻለ ነው ብሎ ያቀረበው አድራሻ ትክክል ከሆነ እባክዎን አማራጩን መርጠው “ያስገቡ እና ይቀጥሉ” የሚለውን ይጫኑ።
  - እርስዎ ያስገቡትን የመጀመሪያውን አድራሻ መቀጠል ከመረጡ እባክዎ አማራጩን መርጠው “ያስገቡ እና ይቀጥሉ” የሚለውን ይጫኑ።

- ሁለቱም አማራጮች ትክክል ካልሆኑና አድራሻዎን ማረም ከፈለጉ እባክዎ አመራጩን ይምረጡና "ተመለስ እና የእኔን ኦርጂናል አድራሻ አርትዕ አድርግ" ይጫኑ።

**የነዋሪነት ጥያቄ**

ምንም እንኳ የትኛውም የዓለማችን ክፍል ሆነው ማመልከት ቢችሉም፣ የ DC የህዝብ ትምህርት ቤት ውስጥ ለመመዝገብ ትክክለኛ ነዋሪ መሆን አለብዎ። የእርስዎ አድራሻ ሜሪላንድ ወይም ቨርጂንያ ከሆነ፣ ወደ ዲስትሪክቱ ለመዛወር እያቀዱ እንደሆነ ይጠየቃሉ።


City | State | Zip Code
Hyattsville | Maryland | 20899

PLEASE NOTE:

You indicated that you currently reside outside of the District of Columbia (DC). Are you planning to move into the District of Columbia by the time you enroll the student for the 2021-22 school year?

1 Yes.
2 I am not sure at this time.
3 I am currently experiencing homelessness, housing unstable, or a Ward of the District.
4 No. I will continue residing at my current (non-DC) address, and have no intent to move into the District of Columbia.

"እባክዎ ያስታውሱ፥
እርስዎ ባሁን ጊዜ ከኮሎምቢያ ዲስትሪክት (DC) ውጭ እንደምኖሩ አመልክተዋል። ተማሪውን ለ2021-22 የትምህርት ዓመት በሚያስመዘግቡበት ጊዜ ወደ ኮሎምቢያ ዲስትሪክት ለመዛወር አቅደዋል?"

1 አዎ

2 በዚህ ጊዜ እርግጠኛ አይደለሁም።


3 እኔ ባሁን ጊዜ የጎዳና ተዳዳሪነት፣ ያልተረጋጋ የመኖርያ ቤት ሁኔታ፣ ወይም የዲስትሪክቱ ዋርድ ነኝ።

4 አይ፣ ያሁኑ አድራሻየ (DC-ያልሆነ) ውስጥ መኖር እቀጥላለሁ፣ እና ወደ ኮሎምቢያ ዲስትሪክት ለመዛወር ዓላማ የለኝም።

ወደ DC ለመዛወር እያቀዱ ወይም እያሰቡ ከሆነ፣ የDC አድራሻ የሌለው የ My School DC ማመልከቻን ማስገባት ይችላሉ። ይሁን እንጂ፣ በ DCPS ትምህርት ቤቶች ውስጥ የድንበር-ውስጥ ወይም የቅርበት አማራጩን አያገኙም።
በሎተሪ አማካኝነት ከትምህርት ቤት ጋር ከተዛመዱ፣ በምዝገባ ቀነ-ገደብ ውስጥ በትምህርት ቤቱ መመዝገብ አለብዎ ወይም በተዛመዱበት ትምህርት ቤት በታዎን ያጣሉ። በታዎን ለመቀበል አስፈላጊ የሆኑ የምዝገባ ቅጾችን ማስገባት እና የ DC ነዋሪነትን ማስረዳት ይጠይቃል።
ወደ DC ለመዛወር እቅድ የሌሎት ቢሆንም እንኳን ለ DC ትምህርት ቤቶች ማመልከት ይችላሉ፣ ይሁን እንጂ፣ ሁሉም የ DC (ወይም የሚመጡ የ DC) ነዋሪዎች ቅድሚያ ያገኛሉ። እርስዎ የ DC ነዋሪ ካልሆኑ እና የምደባ ወይም የተጠባባቂ ዝርዝር ግብዣ ከተቀበሉ፣ተማሪው ትምህርት ለመጀመር ብቁ እንዲሆን ከ OSSE ጋር የትምህርት ክፍያ ስምምነት ማድረግ እና የመጀመሪያ የትምህርት ክፍያ መክፈል አለብዎ። የመጋቢ መብቶችን ለመቀበል ብቁ የሚሆኑት የ DC ነዋሪዎች ብቻ ናቸው። DC ነዋሪ ያልሆኑት ካሁኑ ትምህርት ቤታቸው የመጨረሻ ክፍል በኋላ የመጋቢ ንድፍ ውስጥ ለመቀጠል ዳግም ማመልከት ይኖርባቸዋል።

**ተጨማሪ መገናኛ (በፍላጎት የሚደረግ)**


ተጨማሪ ተጠሪ ማከል አማራጭ ነው። የተማሪውን ማመልከቻ በተመለከተ ጥያቄ ካለ እና ወደ ዋናው አሳዳጊ መድረስ ካልቻልን ተጨማሪው ተጠሪ ጠቃሚ ነው።




አስፈላጊውን መረጃ ሁሉ ካሰገቡ በኋላ “ያስገቡ እና ይቀጥሉ” የሚለውን ተጭነው ማመልከቻውን ወደፊት ለመቀጠል ወይም ማመልከቻውን ተመልሰው ለመጨረስ “ያስገቡ እና ቆይተው እንደገና ይመለሱ” የሚለውን ይጫኑ።

## ደረጃ 7፡ ትምህርት ቤቶችን መምረጥ

አመልካች እስከ 12 ት/ቤቶች ድረስ መምረጥ ይችላሉ። የሚፈልጉትን ት/ቤት ከመረጡ በኋላ “ያስገቡ እና ይቀጥሉ” የሚለውን በመጫን ማመልከቻውን ወደፊት ለመቀጠል ወይም ደግሞ “ያስገቡ እና ቆይተው እንደገና ይመለሱ” የሚለውን በመጫን እስካሁን የሰሩትን ማመልከቻ ማስገባትና ቆይተው ሊመለሱ ይችላሉ።




**ማስታወሻ፤** የአመልካቹ በክልል ውስጥ ያለ ት/ቤት በስተግራ በኩል ይታያል። የአመልካች በክልል ውስጥ ያለ የDCPS ትምህርት ቤት የሚወሰነው ዋና አሳዳጊ በማመልከቻው ላይ በሞላው አድራሻ ነው። አመልካቹ ከK-12 ክፍሎች ላይ የሚያመለክት ከሆነ፣ ከአመልካቾች በወሰን ውስጥ ያለ ወይም የመዘዋወርያ ትምህርት ቤቶችን በትምህርት ቤት ምርጫ ዝርዝሮች ውስጥ አያዩትም፣ ምክንያቱም በቀጥታ እነዚህ ትምህርት ቤቶች ላይ መግባት ይችላሉ።

ሆኖም፣ አመልካቾች በክልላቸው በሚገኝ  የDCPS ትምህርት ቤት PK3 ወይም PK4 ገብቶ መማር ከፈለጉ በMy School DC አማካይነት ማመልከት አለባቸው። በክልል ውስጥ ያለው ትምህርት ቤታቸው ከተዘረዘሩት ውስጥ አማራጫቸው ሊሆን ይችላል፣ እና በወሰናቸው ውስጥ ላለ ትምህርት ቤት ሲያመለክቱ "የክልል ውስጥ ምርጫ" ያገኛሉ።



**የወንድም/እህት ምርጫ፤**


አመልካቹ በማመልከቻው መጀመሪያ ላይ በት/ቤት ወንድም ወይም እህት እንዳላቸው ካመለከቱ እና አመልካቹ በማመልከቻቸው ላይ ያንኑ ትምህርት ቤት ከመረጡ፣ የወንድም/እህት አማራጮች በራስ ሰር በዚያ ትምህርት ቤት ይጠየቃሉ።




ማመልከቻዎን ካስገቡ በኋላ ትምህርት ቤቱ ወንድም/እህት በትምህርት ቤቱ የተመዘገበ መሆኑን በማረጋገጥ የወንድም/እህት ምርጫው እንዲፀድቅ ያደርጋል።

አመልካቹ በመኖሪያ ክልል ውስጥ ለሚገኙ የPK3/PK4 የዲሲ የህዝብ ት/ቤት (DCPS) ፕሮግራም የሚያመለክት ከሆነ እና በወቅቱ በK-12 ባሉት ክፍሎች ውስጥ የሚማር ወንድም/እህት ከሌለው ግን በመጪው የትምህርት ዘመን የሚመዘገብ ወንድም/እህት ካለው የወንድም/እህት ምርጫ መጠየቅ ይችላል። ይህንን ለማድረግ ወደ የተማሪ መረጃ ክፍል ይመለሱ፣ (አቋራጭ: በዚህ ገጽ ላይ ከላይ ቁጥር #1ን ይጫኑ) ከትምህርት ቤቱ ስም በስተቀኝ በሚገኘው ሰማያዊ ሳጥን ውስጥ ምልክት አድርጉ እና በክልል ውስጥ የሚማረውን ወንድም/እህት ስም፣ ክፍል (የገባው ክፍል ከK-12 ባሉት ክፍሎች ውስጥ መሆን አለበት)፣ እንዲሁም "0000000" ለተማሪው መታወቂያ ይጻፉ። <u>የተማሪው መታወቂያ ተቀባይነት እንዲኖረው ሰባት ዜሮዎች እንዲኖሩት ያስፈልጋል።</u> ለመጪው የትምህርት ዘመን የወንድም/እህት ምርጫ ለማግኘት ወንድም/እህት በክልል ውስጥ ባለ ትምህርት ቤት መግባት አለባቸው።


**ካርታ፣ ከቤት ያለው ርቀት፣ ባለፈው ዓመት የቀረቡ ቦታዎች ቁጥር እና ልዩ መስፈርቶች**





ትምህርት ቤት ሲመርጡ፣ ከቤትዎ ያለው ርቀት (ይህም በአሳዳጊው ክፍል ያስገቡት አድራሻ) በራስ ሰር ይሰላል። እንደዚሁም ለዛ ክፍል ለዛ ትምህርት ቤት ባለፈው ዓመት በሎተሪ የተሰጡ ክፍት ቦታዎች ቁጥር ይታያል። በተጨማሪ፣ አንዳንድ ት/ቤቶች በቀይ ጽሑፍ የደመቁ ልዩ ልዩ መስፈርቶች አሏቸው። ልዩ መስፈርቶቹን ለመረዳት እርዳታ የሚፈልጉ ከሆነ፣ እባክዎን ወደ My School DC Hotline በስልክ ቁጥር (202) 888-6336 ይደውሉ።

## ደረጃ 8፡ የ DCPS ምርጥ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና መርሀግብሮች

ልጅዎ ለDCPS ምርጥ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም መርሀግብር የሚያመለክት ከሆነ ማመልከቻውን ለማስገባት ከመቻላቸው በፊት ተጨማሪ መረጃዎችን ማቅረብ ይኖርባቸዋል። ምርጥ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና መርሀግብሮች ላይ ለማመልከት ምን እንደሚያስፈልግ የበለጠ ለመረዳት፣ MySchoolDC.orgን ይጎብኙ ወይም ወደ My School DC ነጻ የስልክ ቁጥር (202) 888-6336 ይደውሉ።




1. እያንዳንዱን ምርጥ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማመልከቻ ገጾችን ለመመልከት በገጹ መጀመሪያ በሚገኘው ሰንጠረዥ ላይ የትምህርት ቤቱን ስሞች በመጫን መመልከት ይችላሉ።
2. የሚፈለገውን ዝርዝር ጉዳይ አሟልተው እንደሆነ የሚያሳይ የሂደት ቻርት።
3. <u>አማራጭ:</u> ተጨማሪ ትምህርት ቤቶችን ለማከል ወይም ትምህርት ቤቶችን ከዝርዝርዎ ማስወገድ ከፈለጉ "የትምህርት ቤት ምርጫዎችን ያርሙ" ላይ ጠቅ ያድርጉ።



**መደበኛ የፈተና ውጤቶች**

የ DCPS ተመራጭ ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች ለ 2021-2022 ትምህርት ዓመት ደረጃውን የጠበቀ የፈተና ነጥቦችን አይጠይቁም።

**የሪፖርት ካርዶችን ይጫኑ**

አሁን ካለው የትምህርት አመት ውስጥ የቅርብ ጊዜው የሪፖርት ካርድዎ እና ከቀዳሚው ዓመት የመጨረሻ ሪፖርት ካርድ (ከሁሉም የማርክ ጊዜዎች ደረጃዎችን የሚያጠቃልል) በየትኛውም ምርጥ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለማመልከት አስፈላጊ ነው። እነዚህን የሪፖርት ካርዶች በማመልከቻዎ ላይ መጫን አለብዎት።


- ማስታወሻ፡ እርስዎ ባሁን ጊዜ የ DCPS ትምህርት ቤት ውስጥ ተመዝግበው ከሆነ እና ማመልከቻው ውስጥ መጀመሪያ ላይ የተማሪ መታወቂያ ካርድ# አቅርበው ከሆነ፣ የሪፖርት ካርድዎ ወዲያውኑ ይጫናል። የሚታየው የቀይ የፋይል ስምን በመጫን የእርስዎ ሪፖርት ካርዶች እንደተሟሉ ደግመው ያረጋግጡ። የሪፖርት ካርድዎ ትክክል እንዳልሆነ ወይም ያልተሟላ እንደሆነ ካሰቡ፣ እባክዎ የትምህርት ቤቱ ሬጅስትራር ወይም የ DCPS ማእከላዊ ቢሮ ውስጥ shyra.greogory@k12.dc.gov ያግኙ።
- ሌሎች ሁሉም አመልካቾች የ "ፋይል ይምረጡ" አዝራርን ተጠቅመው የሪፖርት ካርዶቻቸውን መጫን አለባቸው።
- ሊጫኑ የሚችሉት የፒዲኤፍ ፋይሎች ብቻ ናቸው።
- የልጅዎ ት/ቤት አማካሪ እርስዎን በመወከል እነዚህን ሰነዶች መጫን ይችላል። ሆኖም፣ አንድ ሰው (ወይም እርስዎ ወይም አማካሪዎ) የሪፖርት ካርዶችን ካልጫኑ ማመልከቻው ገቢ ሊደረግ አይችልም።

የሪፖርት ካርዶች ለአሁኑ የDCPS ተማሪዎችን ብቻ በራስ ሰር መሰቀል አለባቸው። ልጅዎ የአሁኑ የDCPS ተማሪ ከሆነ እና ይህን መረጃ የማያዩ ከሆነ፣ እባክዎን My School DC Hotline በስልክ ቁጥር (202) 888-6336 ደውለው ያነጋግሩ።


## ደረጃ 9፡ የትምህርት ቤት ምርጫዎን ቅደም ተከተል መስጠት

በዚህ ክፍል ውስጥ፣ አመልካቾች የሚመርጧቸውን ትምህርት ቤቶች መሰርት ምርጫቸው በቅደም ተከተል (ለምሳሌ፣ 1ኛ ምርጫቸውን፣ 2ኛ ምርጫቸውን፣ 3ኛ ምርጫቸውን፣ ወዘተ...) ያስቀምጧቸዋል። አመልካቾች ትምህርት ቤቶችን የሚያስቀምጡበት ቅደም ተከተል ወሳኝ ነው። ሎተሪው አመልካቾችን መጀመሪያ ከ1ኛ ምርጫቸው፣ ቀጥሎ ከ2ኛ ምርጫቸው እያለ በመቀጠል ለመመደብ ይሞክራል። ተማሪዎች ከአንድ ትምህርት ቤት በላይ አይመደቡም፣ እንዲሁም በተጠባባቂነት የሚቆዩበት ትምህርት ቤት ከተመደቡበት ትምህርት ቤት ከፍተኛ ደረጃ ያለው ይሆናል።ይህ በማመልከቻው ሂደት ወሳኝ እርምጃ ነው። አመልካቾች ትምህርት ቤቶቻቸውን በጣም በሚመርጡት መሰረት ቅደም ተከተል ደረጃ መስጠት አለባቸው።

እባክዎን ለትምህርት ቤት ምርጫዎ ደረጃ ይስጡ




As you select your schools additional information will appear below each school choice.





ከዚህ ትምህርት ቤት ጋር የሚዛመዱ ከሆነ፣ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በመጠባበቂያ ዝርዝር ውስጥ አይያዙም።

ከዚህ ትምህርት ቤት ጋር የሚዛመዱ ከሆነ ከዚህ ትምህርት ቤት በላይ በተዘረዘሩትት/ቤቶች ብቻ በመጠባበቂያ ዝርዝር ውስጥ ይያዛሉ፣ ከዚህ ትምህርት ቤት በታች ካመለከቱት ማንኛቸውም ትምህርት ቤቶች ውስጥ በተጠባባቂነት አይያዙም።

ከዚህ ትምህርት ቤት ጋር የሚዛመዱ ከሆነ ከዚህ ትምህርት ቤት በላይ በዘረዘሯቸው ት/ቤቶች በመጠባበቂያ ዝርዝር ውስጥ ይያዛሉ።.

አንዴ ለሁሉም ት/ቤቶች ደረጃ ከሰጡ በኋላ፣ ማመልከቻውን ለማስቀመጥ እና ወደፊት ለመሄድ “ያስቀምጡ እና ይቀጥሉ” የሚለውን ወይም ለማስቀመጥ እና ቆየት ብሎ ለመመለስ "ያስገቡ እና ቆይተው እንደገና ይመለሱ" የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።

**የደረጃ ቅደም ተከተል ማረጋገጫ መልዕክት**
**“ያቀምጡ እና ይቀጥሉ” የሚለው ላይ ጠቅ ካደረጉ የትምህርት ቤት ምርጫዎትን እንዴት በደረጃ እንዳስቀመጡ እርግጠኛ ለመሆን አንድ መልዕክት ይታያል።**





መልዕክቱ እንዲህ ይላል፣ "ከአንድ ትምህርት ቤት ጋር ብቻ ሊዛመዱ ይችላሉ። የተዛመዱ ከሆኑ ከተዛመደው ትምህርት ቤት ስር በደረጃ በተቀመጡት ማንኛውም ትምህርት ቤቶች በተጠባባቂነት አይያዙም። ት/ቤትዎችዎን እርስዎ በሚመርጧቸው ቅደም ተከተል ደረጃዎች መቀመጣቸውን እርግጠኛ ነዎት?"

ይህን መልዕክት ካዩ ሁለት አማራጮች አለዎት፡

- አማራጭ 1፡ የትምህርት ቤት ምርጫዎን በቅደም ተከተል ያስቀመጡበትን መንገድ ለመገምገም ወይም ለመቀየር ከፈለጉ “አይ፣ የእኔን ደረጃ መለወጥ እፈልጋለሁ” የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።
- አማራጭ 2: ምንም አይነት ለውጦች ማድረግ ካልፈለጉ “አዎ፣ ወደ ቀጣዩ ደረጃ ቀጥል” የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።


## ደረጃ 10፡ ማረጋገጥና ማስገባት




የሚከተሉትን ያረጋግጡ፤

- **የተማሪ መረጃ**
    1. የተማሪው ስም፤
    2. የትውልድ ቀን
    3. ጾታ
    4. የአሁኑ የክፍል ደረጃ
    5. የአሁኑ ትምህርት ቤት
    6. የመጪው የጸደይ የክፍል ደረጃ
    7. የወንድም/እህት መረጃ
        a. የወንድም/እህት ስም
        b. የወንድም/እህት የክፍል ደረጃ
        c. የተማሪ የመታወቂያ ቁጥር
        d. የወንድም/እህት ትምህርት ቤት

ማንኛውንም ማስተካከያ ለማድረግ “የተማሪን መረጃ አርትዕ ያድርጉ” ላይ ጠቅ ያድርጉ።




**የአሳዳጊ መረጃ**

8. የአሳዳጊ ስም
9. ተመራጭ ቋንቋ
10. አድራሻ
11. የስልክ ቁጥር 1
12. ስልክ ቁጥር 2 (አማራጭ)
13. የኢሜይል አድራሻ

**ተጨማሪተጠሪ**(ማስታወሻ:ከ15-20ያሉትመረጃዎችእርስዎካቀረቧቸውብቻይታያሉ)


14. ተጨማሪተጠሪስም
15. ተመራጭ ቋንቋ
16. አድራሻ
17. የስልክ ቁጥር 1
18. የስልክ ቁጥር 2
19. የኢሜይል አድራሻ

ማንኛውም ማስተካከያ ለማድረግ "የአሳዳጊ መረጃን አርትዕ ያድርጉ" ላይ ጠቅ ያድርጉ።

**የትምህርት ቤት ምርጫ እና የደረጃ ቅደም ተከተል አሰጣጥ**

“የእኔን ትምህርት ቤት ምርጫዎች አርትዕ ያድርጉ” የሚለውን ጠቅ በማድረግ ትምህርት ቤቶችን መጨመር ወይም ማስወገድ ይችላሉ።
የትምህርት ቤት ደረጃ አሰጣጥዎን ለማዘመን ከፈለጉ “የትምህርት ቤት ደረጃን አርትዕ ያድርጉ" የሚለውን ጠቅ ማድረግ ይችላሉ።




**ያረጋግጡ እና ይፈርሙ**

20. ከዚህ ተማሪ ጋር ባለው ግንኙነት ውስጥ እርስዎ ማን ኖት?
    - ወላጅ

- አሳዳጊ
- አያት
- አክስት/አጎት
- የማህበራዊ ኑሮ ሰራተኛ/ካውንስለር
- እኔ ተማሪው ነኝ
- ሌላ

21. ውጤቶችን በፖስታ ለመቀበል ይፈልጋሉ? (አዎ ወይም አይ)
22. 22. ይህን አንቀጽ ሙሉውን ያንብቡ፤ በማመልቻው ወደፊት ለመቀጠል ሳጥኑ ውስጥ ምልክት ማድረግ አለብዎት። (ይህን ቋንቋ አክል፤ "ይህ መልዕክት እንዲህ ይላል" የሚለውን አስወግድ) "እስከማውቀው ድረስ የሰጠሁት መረጃ በሙሉ ትክክለኛ መሆኑን አረጋግጣለሁ። እውነተኛ ያልሆነ ወይም የተሳሳተ ማስረጃ ማስገባት ከምርጫ እንደሚያስወጣኝ እና ማመልከቻው ውድቅ እንደሚሆን መገንዘቤን አረጋግጣለሁ። በተጨማሪም በትምህርት ቤቱ ከገባሁ በኋላ የትምህርት ቤቱን ህግጋት ማክበር፣ የMy School DC Seat የቅበላ ቅጽ መሙላት፣ የዲሲ መኖሪያ መረጃ ማቅረብን ጨምሮ ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎችን በማቅረብ ማክበር እንዳለብኝ ማወቄን አረጋግጣለሁ።"
23. ስምዎን በመጻፍ ማመልከቻውን ይፈርሙ
24. ቀኑ ይወጣል
25. የሚከተሉትን መግለጫዎች ያንብቡ፡
    a. ለቅበላ የተወሰኑ የአካዳሚያዊ መመዘኛዎች የሚያስፈልጋቸው ለDCPS ምርጥ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወይም ፕሮግራሞች ካልሆነ በስተቀር በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ ለመግባት የትምህርት/የአካዳሚክ ወይም የአትሌቲክስ ብቃት ተጽዕኖ አይፈጥርም። እንደዚህ ዓይነቶቹ መመዘኛዎች ለሁሉም ተማሪዎች በአንድ ወጥነት ይተገበራሉ።
    b. My School DC በዘር፣ በቀለም፣ በብሄራዊ ማንነት፣ በፆታ፣ በእድሜ፣ በአካል ጉዳት፣ በሃይማኖት፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በመልክ፣ በጾታዊ ዝንባሌ፣ በቤተሰብ ኃላፊነት፣ በአካል ጉድለት፣ በአስተማሪነት ወይም በፖለቲካ ወገንተኝነት ላይ ተመስርቶ በፕሮግራሞቹ እና እንቅስቃሴዎቹ ላይ አድልዎ አያደርግም። መድልዎ የሚታለፍ አይሆንም እናም በመድሎ ውስጥ የሚሳተፉ ሰዎች ለቅጣት እርምጃ ይዳረጋሉ።
    c. በዚህ ማመልከቻ ላይ የቀረበው መረጃ የጋራ ሎተሪን ለማሻሻል ለግምገማ እና የእቅድ አወጣጥ ዓላማዎች እንደ ተመራማሪ ካሉ ሶስተኛ ወገኖች ጋር ሊጋራ ይችላል። የተማሪ እና የአሳዳጊ መረጃ ለሕዝብ ይፋ አይደረግም።

ማመልከቻዎን ለማስገባት "Submit Application" ላይ ጠቅ ያድርጉ። ማመልከቻውን ለማስቀመጥ እና በኋላ ላይ ለመመለስ "Save and Come Back Later" የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።

ማመልከቻዎን ሲያስገቡ ወዲያውኑ የማመልከቻ ክትትል ቁጥርን ይቀበላሉ። ሲመዘገቡ በኢሜል አድራሻ ተጠቅመው ከሆነ ወይም በማንኛውም በታ ውስጥ የኢሜል አድራሻ አቅርበው ከሆነ ይህ ቁጥር በኢሜይልም ይላክልዎታል። እርዳታ ለማግኘት ወደ My School DC Hotline የሚደውሉ ከሆነ ይህን ቁጥር ይጥቀሱ። የቀጥታ የስልክ መስመሩን በ (202) 888-6336 ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ8am እስከ 5pm ማግኘት ይቻላል።

ከላይ በግራ ጥግ ላይ "Start a New Sibling Application" አዝራርን ጠቅ በማድረግ በቤተሰብዎ ላለ ሌላ ልጅ አዲስ ማመልከቻ መክፈት ይችላሉ። በአካውንትዎ ውስጥ ያሉት ሁሉም አመልካቾች ወንድማማቾች እና እህቶች መሆን አለባቸው።

## ማመልከቻዎን ማረም





**ያልተሟሉ ማመልከቻዎች**

ማመልከቻውን ከማስገቢያው የመጨረሻ ቀን በፊት ማመልከቻዎን ማረም ወይም መደምሰስ ይችላሉ።

ወደ አካውንትዎ በመለያ ሲገቡ የእኔ ማመልከቻዎች ማጠቃለያ ገጽን ያያሉ።

በማመልከቻዎ ላይ መስራቱን ለመቀጠል “ማመልከቻን አርትዕ ያድርጉ” አዶን ጠቅ ማድረግ ይችላሉ። እንዲሁም ማመልከቻዎን ለመሰረዝ “ማመልከቻን ሰርዝ” የሚለው አዶ ጠቅ ማድረግ ይችላሉ።

ማመልከቻዎን ከ“የማመልከቻ ማስገቢያ ቀነ ገደብ” በፊት ማስገባትዎን ያረጋግጡ።




እንደዚሁም በዚህ ዓመት My School DC አጭር፣ በምርጫ የሚደረግ፣ የዳሰሳ ጥናት በማድረግ የማመልከቻ ሂደቱን ሙሉ ለቤተሰቦች በተሻለ ሁኔታ እንዴት እንደምናግዝ ለማወቅ አመልካቾች My School DC እንዲያግዙ ዕድሉን ይሰጣል።

የዳሰሳ ጥናት ጥያቄዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

1. የ My School DC ማመልከቻ መሙላት ላይ ያለዎትን ተሞክሮ ደረጃ ይስጡት?
   - በጣም ቀላል (5)
   - ቀላል (4)
   - ከሞላ ጎደል ቀላል (3)
   - አስቸጋሪ (2)
   - በጣም አስቸጋሪ (1)
2. በሎተሪ ውስጥ የመጨረሻ አንድ ትምህርት ቤት ላይ ብቻ ሊዛመዱ እንደሚችሉ ተረድተዋል?
   - አዎ
   - አይ
3. እንዲያጠናቅቁት እና እንዲረዱት ለእርስዎ ቀላል እንዲሆን My School DC ማመልከቻው ላይ ምን መቀየር ይችላል?

አንዴ ሦስት ጥያቄዎችን ካጠናቀቁ  በኋላ “ዳሰሳ ጥናት አስረክብ” የሚለውን መንካት አለብዎ


## የገቡ ማመልከቻዎች

የማመልከቻዎ ቀነ ገደብ ከማለቁ በፊት ያስገቡትን ማመልከቻ በማንኛውም ጊዜ ማረም ወይም መደምሰስ ይችላሉ።

ወደ አካውንትዎ በመለያ ሲገቡ የእኔ ማመልከቻዎች ማጠቃለያ ገጽን ያያሉ።

ማድረግ የሚችሉት:

1. ማመልከቻዎን ማረም
2. ማመልከቻዎን መደምሰስ
3. የትምህርት ቤት ደረጃዎቹን ማረም
4. የምርጫዎን ሁኔታ ማየት
5. ማመልከቻዎን ማየትና ማተም
6. ለምርጥ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቤቶች) ማመልከቻ ካስገቡ በማመልከቻው ምርጥ የDCPS ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክፍል አስተያየት እንዲሰጡልዎት ለጠይቋቸው የስጧቸውን ማንኛውንም ኢሜሎች፣ የአስተያየትዎ ሁኔታ ምን ላይ እንደሚገኝ ማየት ወይም ማረም። ይህ አዶ የሚታየው ለምርጥ ትምህርት ቤት(ዎች) ካመለከቱ ብቻ ነው።




**ጥያቄዎች? ማመልከቻዎን ለመሙላት እርዳታ ይፈልጋሉ? የMy School DCን አፋጣኝ መስመር በ(202) 888-6336፣ ከሰኞ እስከ አርብ ከ8am እስከ 5pm ይደውሉ። ከአስተርጓሚ ጋር የሚሰራ ወኪል በቋንቋዎ ይረዳዎታል።**